የደውል ድምጽ

ለዋሒድ ዑመር

ሐሳዊው ማን ነው?

የእምነትና የእውቀት ጉልላታቸው ቁልቁል ወርዶ የተፈረካከሰባቸው ፍርስራሹን ለመገንባት እየተቀባበሉ አንድና ተመሳሳይ ነገር ያወራሉ። አንዱ መልስ ይሆንልኛል ብሎ የተናገረውን ሌላው እንደራሱ ይደግመዋል፤ አሁን ባለተራው ዋሒድ ሆኗል፣ የሚቀጥለው ማን ይሆን? አብረን እናያለን። ሰሞኑን ረምላ (የአሸዋ ቅንጣት) የተባለች አብዱሊት "የደወል ድምጽ" በሚል ርዕስ የዋሒድን መጣጥፍ አስነብባናለች፤ ስንቶቻችሁ እንዳያችሁ አላውቅም። ምናልባት ጽሑፉን ዘግይተው ካዩት መካከል ልሆን እችላለሁ። ርዕሱን እንዳየሁት ቀደም ብሎ ብዙ የተባለበት ርዕሰ ጉዳይ ስለሆነ እንዳረጀ እንዳፈጀ ተመልክቸው ላልፈው ነበር። ዋሒድ ሞጋቾቹን "ሐሳውያን" በማለት ሲወርፋቸው እንዲሁ ማለፍ አልፈለግኩም፤ ሐሳዊው ማን እንደሆነ ላሳየው ተሰየምኩ። በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ ጥያቄ ያነሱ ሁሉ ሐሳውያን አይደሉም። ጥያቄያቸውን መመለስ አለመቻል አንድ ነው፤ ሁሉም መልስ የለውም። ምናልባት መልሱ አምኖ መቀበል ሊሆን ይችላል። ያለምንም ጭማሬና ቅናሽ ሌላው የተናገረውን እየደገሙ ጠያቂን መወረፍ ግን "ሐሳዊውን" በትክክል መግለጥ ነው። እናም ሐሳዊው ራሱ ዋሒድ ለመሆኑ አስረጅ አንድ ሁለት እያሉ ማንሳት ይቻላል፡-

1. **ትክክለኛ የጥያቄያቸውን ጭብጥ ወደ ጎን በማድረግ ያልተባለን እንደተባለ አድርጎ ማቅረብ ሐሳዊነት ነው**

ከ"እንደ ደወል ድምጽ" ጋር ተያይዞ ለሚነሳው ጥያቄ የሚጠቀሱት ዋና ዋና ሐዲሶች እነዚህ ብቻ አይደሉም፤ አንዱና ዋነኛውን ለምን አልጠቀሰም? እንዲሁም የጥያቄያቸውም ጭብጥ ደወል የሚባለው ቁስ አይደለም። "እንደ" የምትለው ቃል ትኩረት እንዲደረግባት የተፈለገው የጥያቄውን ጭብጥ ለማዛባት ስለተፈለገ ብቻ ነው። ይህ ከሐሳዊ ይጠበቃል። ጥያቄው ወደ ነቢዩ ሙሐመድ ለ20 ወይም 23 ዓመታት ከዋሸ የጀመረ ይመላለስ የነበረው አካል ማንነት ላይ ነው። ለ20 ወይም 23 ዓመታት ያልኩት የኢስላም ሊቃውንት ቁርአን ለስንት ዓመት ያህል እንደወረደ በዘመኑ ቁጥር ስለማይስማሙ ነው። ለጥያቄው መነሻ የሆኑት ሐዲሶች አንደኛው "ኢማም ቡኻሪይ መጽሐፍ 1, ሐዲስ 2" ሲሆን ሁለተኛው ሐዲስ ደግሞ የሚገኘው በተፍሲር ኢብን ከሢር ውስጥ ነው። እንዲህ ይነበባል፡-

ተፍሲር ኢብን ከሢር ሱረቱል አል-ሒጅር 15 ፡ 34-37

ሳኢድ ቢን ጁቤይር ሲናገር አላህ ኢብሊስን (ሰይጣንን) በረገመው ጊዜ **‘<u>መልኩ ከመላዕክት ወደተለየ መልክ ተቀየረ፣ ድምጹም እንደ ደወል ድምጽ ሆነ።።’</u>** በዚህም ምድር ላይ እስከ ትንሳኤ ቀን ድረስ የሚሰማ ማንኛውም የደወል ድምጽ የዛው የሰይጣን ድምጽ አካል ነው።።

እንደ ልማዳቸው ሐዲሱ ደኢፍ ነው እንዳይሉ የዚህ ሐዲስ አስተላላፊ በትክክለኛ ሐዲስ አስተላላፊነት የሚታወቀው ሳኢድ ቢን ጁቤይር ነው።። ሰውየው ለሙስሊም 78 ለቡኻሪ ደግሞ 147 ሰሂህ የሆኑ ሐዲሶችን በመስጠት በስሙ አስመዝግቧል።። ከላይ እንደተገለጸው ሌሎቹ ሐዲሶች ሊጠቀሱ የቻሉትም **<u>"...በዚህም ምድር ላይ እስከ ትንሳኤ ቀን ድረስ የሚሰማ ማንኛውም የደወል ድምጽ የዛው የሰይጣን ድምጽ አካል ነው"</u>** ስለሚል ይበልጥ ሐሳቡን ግልጽ ያደርጋል በሚል ነው።። አሁንም ጥያቄው ግን እንደ በ"እንደ ደወል" ዓይነት ድምጽ ለነቢዩ ሙሐመድ መልእክት እየያዘ ይመላለስ የነበረው አካል ማን ነው? የሚለው ነው።። ምክንያቱም የሚከተለው ዓይነት ምስልስሎሽ አለና፡-

ተፍሲር ኢብን ከሢር ሱረቱል አል-ሒጅር 15 ፡ 34-37

ሳኢድ ቢን ጁቤይር ሲናገር አላህ **<u>"መልኩ ከመላዕክት ወደተለየ መልክ ተቀየረ፣ ድምጹም እንደ ደወል ድምጽ ሆነ"</u>**።። በዚህም ምድር ላይ እስከ ትንሳኤ ቀን ድረስ የሚሰማ ማንኛውም የደወል ድምጽ የዛው የሰይጣን ድምጽ አካል ነው።።

ለነቢዩ ሙሐመድ ራዕይ የሚያወርደው አካልም ድምጹ ልክ እንደ ሰይጣኑ ሆኖ ተገኘ፡-

ሳሂህ አል-ቡኻሪ ቅጽ 1፣ 1 ፡ 2

አል-ሃሪስ ቢነ ሂሻም ነቢዩን እንዲህ ሲል ጠየቃቸው፡- ራዕዩ ሲወርድ የሚመጣለዎት በምን ሁኔታ ነው? እርሳቸው ሲመልሱም መልአኩ አንዳንድ ጊዜ **<u>"የደወል ድምጽ በሚመስል ድምጽ እየተናገረ ይመጣል"</u>**፤ ይህ አይነቱ የራዕዩ አወራረድ ለእኔ በጣም ልቋቋመው የማልችለው ከባዱ አይነት ነው።። ትቶኝ ከሄደ በኋላ መልአኩ የነገረኝን አስታውሰዋለሁ።። አንዳንዴ መልአኩ ሰው በመምሰል ወደ እኔ ይመጣና ያናግረኛል እኔም ምን እንዳለኝ እረዳለሁ አስታውሰዋለሁም።። አኢሻ አክላም ራእዩ በእርሳቸው ላይ በወረደ ጊዜ ከባድ ብርድ ሰዓት ግንባራቸው ላብ በላብ ይሆናል።።

ስለዚህ ጥያቄው የነቢዩ ሙሐመድ ጅብሪል ማን ነው? የሚል ነው።። ሰይጣንም ድምጹ እንደ ደወል ድምጽ ዓይነት ነው የጅብሪልም እንደ ደወል ዓይነት ነው።። እንዴት ሊመሳሰል ቻለ? ነቢይነታቸውን ካወጁ ከዘመናት በኋላም በመተተኞች ድግምት ጥቃት ይደርስባቸው እንደነበርና ከነቢይም የማይጠበቅ ተግባር ይፈጽሙ እንደነበር በርካታ ሐዲስ አስተላላፊዎች ገልጸዋል፤ እንዴት ሊሆን ቻለ? ነው ጥያቄው።። ምናልባት ሙግት ስለማይታክተው “ድምጹ የክንፉ ነው ብያለሁ” ይል ይሆናል።። ይህንን የቡኻሪ ሐዲስ መፍቻ ወደሆነው ፈቱል ባሪ ሂድና ስለ “እንደ ደወል ድምጹ” የኢስላም ሊቃውንት የሰጡትን የተለያዩ አመለካከቶች ተመልከት።። አንዱ አንተ ያልከው ሲሆን አጠቃላይ

መረጃው ግን አመለካከቱ ስህተት መሆኑን ያሳያል። ያለ ምንም ተጨማሪ ማብራሪያ ሐዲሱ ላይ በግልጽ የሚታየው እንደ ደወል ዓይነቱ ድምጽ ራዕዩ የሚተላለፍበት፣ የመጣው አካል የሚናገርበት እንጂ ሌላ ተጨማሪ ድምጽ እንደሆነ አያሳይም። ራሱ ከተረጎመው ላስነብባችሁ፤ ከክንፍ ጋር የሚያያዝ ምንም ሐሳብ የለውም፡-

> ሓሪሥ ኢብኑ-ሂሻም የአላህ መልክተኛ"" ሆይ **'<u>ወሕይ' እንዴት ነው የሚመጣሎት?</u>** ብሎ ጠየቃቸው፤ የአላህ መልክተኛም፡- **<u>አንዳንድ ጊዜ "እንደ" ደወል ድምጽ አምሳያ ሆኖ ይመጣኛል</u>**። እርሱ በእኔ ላይ በጣም የሚበረታው ሁኔታ ነው፤ ላብም ይወርደኛል፤ **<u>እርሱ የሚለውንም እይዘዋለሁ...</u>**

"ወሕይ እንዴት ይመጣል?" ለሚለው ጥያቄ መልሱ "እንደ ደወል ድምጽ አምሳያ" የሚል ነው። ስለ ክንፍ ስለ ሌላ ድምጽ የሚተርክ ምንም ነገር የለም። እንዲህ ዓይነቱን ወሳኝ ጥያቄ ወደጎን ትቶ ሌላ እንደተባለ ማስመሰል ግን አድማጭ አንባቢን ማጭበርበር ነው፤ የሰይጣን ዓይነት ሐሳዊነትም ነው። መመለስ ከቻለ መመለስ የነበረበት ለዚህ ግልጽ ጥያቄ ነበር።

2. **ነቢዩ ራዕዩን ሲቀበሉ ስለታዩባቸው ምልክቶች ከመጽሐፍ ቅዱስ ነቢያት ጋር በማነጻጸር "ልክ ነበሩ የነቢይ ወጉ ነው" ሊለንም ሞክሯል**

ይህንን ለማስረዳት እንዲህ ነበር ያለው፡-

> ወሕይ ሲመጣላቸው ያልባቸው እንደነበረም እና በሌላ ሐዲስ ፊታቸው ይቀላ እንደነበር ተጠቅሷል፤ ይህ የሚያሳየው ይመጣላቸው የነበረው የአምላካችን የአላህ ቃል እንዴት ከባድ እንደነበረ ቁልጭ እና ፍንትው አድርጎ የሚያሳይ ነው።

በእርግጥ ነቢዩ ራዕይ ወረደላቸው ሲባል የሚታዩባቸው ሁኔታዎች እነዚህ ዋሒድ የገለጣቸው ብቻ እንዳልነበሩ በበርካታ ግለ ታሪክ መዛግብታቸው ተዘግቧል። እነርሱን ብጠቃቅስ እንደለመዱት ነቢያችን ተሰደቡ በሚል አቅጣጫ ሊቀይሩ ስለሚችሉ ሌላም እንዳለ መግለጼ በቂ ስለሆነ ያንን እተወዋለሁ። ይሁንና የቃሉን ክብደት ያሳዩልኛል ብሎ ያሰባቸውን ሁለት የቁርአንን አንቀጾች ጠቅሷል፤ አንደኛው፡-

> 73፥5 እኛ ባንተ ላይ ""ከባድ ቃልን"" እንጥላለንና።

"ከባድ" ያለው ሸክምን ማሳየቱ ከሆነ (መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ሸክም የሚልን ቃል ከአውዱ ገንጥሎ ጠቅሶ ለማነጻጸሪያነት ተጠቅሟል) ስንት ኪሎ ቢመዝን ይሆን እንዲያ ያደርጋቸው የነበረው? "ከባድ" ሲባል ሸክም ከሆነ "አሸከማቸው" እንጂ እንዴት አስተማራቸው ሊባል ይቻላል? ከባድ ቃልን ማለቱንስ የኢስላም ሊቃውንት እንደ ዋሒድ ይሆን የሚፈቱት ወይስ በሌላ መንገድ? ካልሆነ ምን ማለት ነው? ሐሳውያን ቃላትን እነርሱ የሚፈልጉትን ብቻ እንዲናገሩ በመጠምዘዝ ይታወቃሉ። ዋሒድም ያደረገው ይህንኑ ነው፤ ሐሳዊ ነውና። ይህንን የቁርአን አንቀጽ በተመለከተ ማብራሪያ የሰጡ አብዛኞቹ ሊቃውንት የሚያምኑት ክብደቱ ትግበራው እንደሆነ ነው። ምክንያቱም በውስጡ ትእዛዛትንና

ክልከላዎችን፣ በሌሊት ለጸሎት መነሳትን፣ ይህ ደግሞ ለሕግ ተላላፊዎች አስቸጋሪ መሆኑን ለመግለጽ እንደሆነ ያምናሉ። ስለዚህ የዋሒድ ትርጓሜ መሠረተ ቢስ ነው።

ሁለተኛው አንቀጽ ክብደቱን ይገልጽልኛል ብሎ የጠቀሰው እንዲህ ይላል፡-

> 59፥21 ይህንን ቁርኣን በተራራ ላይ ባወረድነው ኖሮ ከአላህ ፍራቻ የተነሳ ተዋራጅ ተሰንጣቂ ኾኖ ባየኸው ነበር፤ ይህችን ምሳሌ ይገመግሙ ዘንድ ለሰዎች እንገልጻታለን።

ይህም ቢሆን ሐሳዊነት ነው፤ ተራራን ሊበታትን የሚችል ነገር ነቢዩ ላይ ያረፈ ከሆነ ዓለት የማይችለውን እንዴት ሥጋ ለባሽ ሊቋቋመው ይችላል? ዓለት የሚበታትን ነገር ወድቆባቸው እንዴት ሊተርፉ ቻሉ? እያወራን ያለው ስለክብደት ስለሆነ ብዬ ነው። ይታመን እንኳ ቢባል ለመታመን በቅድሚያ ቁርአን መለኮታዊ ቃል መሆኑ መረጋገጥ ይኖርበታል። ቁርአን ከሰማይ የወረደ መለኮታዊ ቃል ስለመሆኑ ማስረጃ በሌለበት ሁኔታ "ተራራን ይሰነጥቃል" ብሎ ማለት ሐሳዊነት ነው። ቁርአን ከዚህም ከዚያም የተጠረቃቀመ፣ ጀሮ ሲጠግብ በአላህ ስም የተነገረ ቃል እንጂ ከሰማይ የወረደ መለኮታዊ ቃል አይደለም። ለዚህ እጅግ በርካታ ማስረጃዎችን ማቅረብ ይቻላል፤ የተወሰኑትን እነሆኝ ብያለሁ፡-

1. ሰዎች ቁርአን ተነቦላቸው ከሰሙ በኋላ "ይህማ የቀደሙ ሰዎች ተረት ነው" ብለዋል፤ ከእነዛ መካከል አንዱ የመካው ምሑር አን-ናድር ነው። ይህ ሰው ወደ ታሪካዊቷ በእውቀት ወደ በለጸገችውና የተለያዩ ሃይማኖቶች ወደሞሉባት ወደ ፋርስ ሔዶ ትምህርቶችን ቀስሞ የመጣ የዘመኑ ሊቅ ነበር። ለሳቢያንና ለዞሮአስትሪያን ሃይማኖታዊ አስተምህሮዎች የቅርብ ሰው ነበር። ለዚህ ነበር "የመጀመሪያዎቹ ሰዎች ጽሑፍ ተረቶች እንጂ ሌላ አይደለም" ያለው። ኢስላም ከዛም እንደቃረመ አውቋልና። እንዲህ ብሎ በመናገሩም ምክንያት ነቢዩ በበድር ጦርነት እንደሌሎቹ ተማርኮ እያለ ሌሎቹን በካሳ ሲለቁ የእዝነቱ ነቢይ አሳርደውታል፡-

   ሱራ 8 ፡ 31
   "አንቀጾቻችንም በነሱ ላይ በተነበቡ ጊዜ ፡- በእርግጥ ሰምተናል፤ በሻን ኖሮ የዚህን ብጤ ባልን ነበር፤ ይህ የመጀመሪያዎቹ ሰዎች ጽሁፍ ተረቶች እንጂ ሌላ አይደለም ይላሉ።"

   ተፍሲር ኢብን ከሲር ሱራ 8 ፡ 31፡-

   ("We have heard (the Qur'an); if we wish we can say the like of this.")

   They boasted with their words, but not with their actions. They were challenged several times to bring even one chapter like the Qur'an, and they had no way to meet this challenge. They only boasted in order to deceive themselves and those who followed their falsehood. **It was said that An-Nadr bin Al-Harith, may Allah curse him, was the one who said this**, according

to Sa`id bin Jubayr, As-Suddi, Ibn Jurayj and others. **An-Nadr visited Persia and learned the stories of some Persian kings**, such as Rustum and Isphandiyar. When he went back to Makkah, He found that the Prophet was sent from Allah and reciting the Qur'an to the people. Whenever the Prophet would leave an audience in which An-Nadr was sitting, An-Nadr began narrating to them the stories that he learned in Persia, proclaiming afterwards, "Who, by Allah, has better tales to narrate, I or Muhammad" **When Allah allowed the Muslims to capture An-Nadr in Badr, the Messenger of Allah commanded that his head be cut off before him, and that was done, all thanks are due to Allah.**

2. ሱራ 3 ፡ 49፡- ...እኔ ለናንተ ከጭቃ እንደ ወፍ ቅርፅ እፈጥራለሁ። በርሱም እተነፍስበታለሁ። በአላህም ፈቃድ ወፍ ይኾናል።...

ይህም ከሰማይ የወረደ መገለጥ አይደለም። በዛ ዘመን በአረብኛ የተጻፈ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የልጅነቱ ወራት የሚተርክ የአዋልድ መጽሐፍ ላይ የተወሰደ ነበር። በዛ ዘመን የነበሩ ክርስቲያን የተባሉ ወገኖች ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የልጅነት ታሪክ ከዛ እየወሰዱ ያወሩ ነበር። እርሱም ነቢዩ ሙሐመድ ጋር ይደርሳል። ለዚህም አይደል የመካ ሰዎች "እርሷም በእርሱ ላይ ጧትና ማታ ትነበብለታለች" ያሉት።(ሱራ 25 ፡ 5) ይህንን ለመሥራት ነጅራኖች በዙሪያቸው እንደ ነበሩ፣ ከኢራቅ የመጡ አጀምኛ የሚናገሩ የተባሉ ክርስቲያኖችም እንደነበሩ መርሳት አስፈላጊ አይደለም። ታዲያ ክፍሉ ከዚህ ጀሮ ሲጠግብ ተወስዶ የተነገረ እንጂ ፈጽሞ ከሰማይ የወረደ መለኮታዊ ሐሳብ አይደለም። የአዋልድ መጽሐፉ ወደ እንግሊዝኛ ተመልሷል፤ እኔም ከዛ የወሰድኩትን ላስነብባችሁ፡-

> 36...Then the Lord Jesus said to the boys: The images that I have made I will order to walk. ...And **He had made figures of birds and sparrows**, **which flew when He told them to fly**, and stood still when He told them to stand, and ate and drank when He handed them food and drink...

3. የአብርሃም ወደ እሳት መጣልና ሳይቃጠል የመቅረቱ ታሪክ (ሱራ 21 ፡ 68-69) ረበናተ አይሁድ ለዘፍጥረት መጽሐፍ ማብራሪያ ከሰጡበት መጽሐፍ ተወስዶ በአይሁዳውያን አንደበት ይተረክ የነበር መሆኑንስ ስንቶቻችሁ ታውቃላችሁ? ይህ ብቻ አይደለም ስለጣኦታቱም መሰባበር እዛው የምታገኙት ታሪክ ነው። (Midrash Rabbah, Genesis chapter 38 : 13-14, page 311) ታዲያ ይህም ቢሆን ጀሮ ሞልቶ ሲተርፍ እንደ አዲስ የተወራ እንጂ ከሰማይ የወረደ ታሪክ አለመሆኑ በዘመኑ ለነበሩ እንደ ንጋት ወለል ብሎ ይታወቅ ነበር።

ቁጥር ስፍር የሌላቸውን ኩርጅ የቁርአን አንቀጾችን መጥቀስ ቢቻልም ለናሙና ስለሆነ ይኸው ይብቃን። ስለዚህ ቁርአንን እንዲያ ማካበድ ሐሳዊነት ነው።

ሌላው ግዙፉ የሐሳዊነቱ ማሳያ ከመጽሐፍ ቅዱስ ነቢያት ጋር ለማነጻጸር የሞከረው ነው። የመጽሐፍ ቅዱስ ነቢያት እንዲያ ይሆኑ የነበረው መልእክቱ እንደ ድንጋይ፣ እንደ ተራራ ይከብዳቸው ስለነበር ሳይሆን በተገለጠላቸው ሰማያዊ ክብር ፊት ፍጥረታዊ ማንነታቸው ሊቆም ስላልቻለ ነበር። ከዛም በኋላ ብርታትን እየተቀበሉ በርትተው መልእክታቸውን ይቀበሉ እንደነበር መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል። ነቢዩ ሙሐመድ ከእነዚህ የእግዚአብሔር ነቢያት ጋር በተነጻጻሪነት ሊያቀርባቸው የሚያስችል ምንም መለኪያ የለም። "አለ" ከተባለም ከቀደሙት ነቢያት ጋር በብዙ እንደሚለያዩ ሊታወቅ ይገባል። ከሚለዩባቸው በርካታ ነጥቦች መካከል አንዱ ራዕይ ሲቀበሉ ይሆኑ የነበሩትን ሁሉ ራዕይ መቀበል ከመጀመራቸው በፊት ከሕጻንነታቸው ዘመን ሃሊማ ቤት እያሉ አንስቶ የተለመደ፣ እንደበሽታ፣ በሰይጣን ቁጥጥር ስር እንዳለ ግለሰብ ይታዩበት የነበር መሆኑ ነው። ያኔ እርሳቸው ጣኦት አምላኪ እንደ ነበሩ የታሪክ ድርሳናቶቻቸው ይናገራሉ። ትንሽ ምሳሌዎችን ጥቀስ ካላችሁኝ እነሆኝ፡-

1. ራዕይ ሲወርድላቸው ያዩዋቸው ጓደኞቻቸው ሁሉ የቀድሞ በሽታቸው እንደጀመራቸው ይቆጥሩ ነበር።
2. 35ኛ ዓመታቸው ላይ ለካእባው እድሳት ድንጋይ ሲሸከሙ ሳለ ጥሏቸው ነበር (Ar-Raheeq Al-Makhtum, The sealed Nectar page 82)
3. ከአክስታቸውና ከአጎታቸው ጋር ጣኦት አምልኮ ሔደው እያለ ጥሏቸው ነበር (Sira Ibn sad Volume 1, Parts 1.40.18)
4. ፍየል ጠባቂ ሳሉ ከልጆች ጋር እየተጫወቱ ሳለ ጥሏቸው ነበር
5. የሚጠብቋቸውን ፍየሎች ለጓደኞቻቸው ሰጥተው መካ ሃረሙ አካባቢ ሔደው ሰርግ ጭፈራ እያዩ ሳለ ጥሏቸው ነበር (Ar-Raheeq Al-Makhtum, The sealed Nectar page 82)
6. ሃሊማ ቤት ሳሉ ጥሏቸው ነበር፤ ሐሊማም በሰይጣን እንደተያዙ ስላመነች ወደ እናታቸው መልሳ ወስዳቸዋለች (Ar-Raheeq Al-Makhtum, The sealed Nectar page 74)

ሳሂህ ነኝ!

የጌታ ሰላም ይብዛላችሁ!!